the global voice of
the legal profession®

# የሃሳብ መስጫ ሰነድ የህግ ሙያ ነጻነት በኢትዮጵያ: ዓ.ጠ.ማ. ልዑክ በኢትዮጵያ ያደረራቸው ጉብኝቶች ሪፓርት

**An International Bar Association Bar Issues Commissions**

**በኢትዮጵያ ተልእኮዎች ላይ ዘገባ**

**ኤፕሪል 2020 እ.ኤ.አ.**

**IBA BIC የክልል አማካሪ Dr Cord Brügman,**

**ጋር በመመካከር IBA BIC Chair Dr Péter Köves**

## 1. መግቢያ

በኢትዮጵያ ወደ ዲሞክራሲያዊ እና ሁሉን አቃፊ ወደ ሆነ አስተዳደር የሚደረገው ጉዞ አሁን ያለው አመራር ወደ ስልጣን ከመጣበት ጊዜ (መጋቢት 2010) ጀምሮ ተግባራዊ ባደረጋቸው መጠነ ሰፊ የለውጥ እርምጃዎች ምክንያት አበረታች እመርታዎችን አሳይቷል። ከዚህ ጊዜ በፊት ሃገሪቷ ለሶስት ዓስርተ ዓመታት በቆየና የፓለቲካ ፓርቲዎችን፣ የግል ሚድያ ተቋማትን፣ ሲቪል ማህበራትንና የፍትህ ስርዓቱን እጅጉን ባዳከመ ጨቋኝ ስርዓት ስር ቆይታለች። በጠቅላይ ሚኒስትር ዓብይ አሕመድ የሚመራው አዱሱ መንግስት አካታች ለሆነ ማሕበረሰብ አስፈላጊ የሆኑ ተቋማትን ለማዘመን፣ ለማጠናከርና ዲሞክሪያሳዊ ለማደረግ የሚያስችሉ የህግ ማዕቀፎችን መቅረጽን አላማው ያደረገ መጠነ ሰፊ የለውጥ ፕሮግራም ቀርጾ ተግባራዊ ማድረግ ጀምሯል።

በዚህ የለውጥ ፕሮግራም ሂደት ላይ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ አንድ ነጥብ ቢኖር ሂደቱ የተቀረጸበት መንገድ አሳታፊና ‹ከታች ወደ ላይ‹ ዘይቤን (‘bottom-up apprach’) የተከተለ መሆኑ ነው። በዚህም መሰረት መንግስት ምሁራንን፣ የህግ ባለሙያዎችንና የመንግስት ተወካዮችን ያካተተ 13 አባላት ያሉትና ነፃ የሆነ የህግና ፍትህ ስርዓት ማሻሻያ አማካሪ ምክር ቤት (አማካሪ ምክር ቤት) ሰኔ 2010 ዓ.ም. አቋቋመ። ምክር ቤቱ የሚመራው በቀድሞው የጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኛና በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የተከበሩ የህግ ሊቅ በሆኑት ፕሮፌሰር ጥላሁን ተሾመ ሊቀመንበርነት ሲሆን በስሩ በባለሙያዎችና ከተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች የተውጣጡ ባለድርሻ አካላት በተዋቀሩ የስራ ቡድኖችን (working groups) ያቀፈ ነው። የስራ ቡድኖቹ አባላት የሆኑ ግለሰቦች ስራቸውን የሚያከናውኑት በፍቃደኝነትና ያለክፍያ ሲሆን ከተለያዩ ውይይቶች፣ ህዝባዊ ምክክሮች፣ ማሻሻያዎችና ስምምነት ከተደረሰባቸው በኋላ ለፌደራል ፓርላማ የሚቀርቡ ረቂቅ ህጎችን የማዘጋጀት ሃላፊነት ተጥሎባቸዋል። ይህ ባለድርሻ አካላትን በህግ የማርቀቅ ሂደት ውስጥ ከጅማሮው የማሳተፍ አካሄድ እንደ አሳታፊ የሆነ ህግ የማርቀቅ ሞዴል አለም አቀፍ አድናቆትን ያተረፈ ሲሆን[1] በድርጅታችን ግምገማ መሰረትም ለሞዴሉ ስኬት የአማካሪ ምክር ቤቱና ምክር ቤቱ ህጎችን እንዲወያዩና እንዲያረቁ የመረጣቸው ባለሙያዎች የላቀ ስራ ዋነኛ ምክንያት ሆኖ አግኝተነዋል።

እስካሁን የተደረጉ የህግ ማሻሻያዎች የፀረ ሽብርተኝነት ህግን ማሻሻልን፣ ለግል ሚዲያ የተሻለ ነፃነትን የሚያጎናፅፍ አዲስ የሚዲያ ህግን፣ በ2012ዓ.ም. ይደረጋል ተብሎ የሚጠበቀውን ቀጣዩን ሀገራው ምርጫ የሚገዛ ህግን እንዲሁም በማህበር የመደራጀት መብትን ለማጠናከር የታሰበው አዲስ የበጎ አድራጎትና ሲቪል ማህበራት ህግን ያጠቃልላሉ። ከድርጅታችን ዓላማ አንፃር እጅግ አስፈላጊው ጉዳይእስካሁን የተደረጉ የህግ ማሻሻያዎች በፍትህ ስርዓቱ ላይ የሚነሱ ቅሬታዎችንም ለመመለስ ትኩረት የሰጡ መሆናቸው ነው።

የፍትህ ስርዓቱን ማሻሻል በተለየ ሁኔታ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ነበር። ብዙ ሪፓርቶች እንደሚያትቱት እንዲሁም ድርጅታችን ያያናገራቸው አካላት እንደሚጠቁሙት በህዝብ ዘንድ ፍትህ ስርዓቱ የሙስናና የመድሎ ችግር እንዳለበት በሰፊው ይታመናል። ለነዚህ ችግሮች መፍትሄ መስጠት እጅግ አስፈላጊ የሆነ ጉዳይ ነው።

ምክንያቱም በፍትህ ስርዓቱ ውስጥ የሙስና መስፋፋት በሌሎች ዘርፎች ሙስናን ለመዋጋት የሚደረጉ ጥረቶችን ስለሚያስተጓጉል፣ የህግ የበላይነትን ስለሚያዳክምና አዎንታዊ የኢኮኖሚ እድገትን ስለሚያስተጓጉል ነው።[2]

---

[1] የተባበሩት መንግስታት ድርጅት አመለካከት የመያዝና የመግለፅ ነፃነት ልዩ ራፓርተር፣ የጉብኝት ሪፓርት (2019 እ.ኤ.አ.) ፣ www.ohchr.org/EN/NewsEvents/Pages/ DisplayNews.aspx?NewsID=25402&LangID=E: (በመጠረሻ የታየው : ማርች 26, 2020 እ.ኤ.አ)

[2] Cf. የአለም ባንክ (2012 እ.ኤ.አ.). *Diagnosing Corruption in Ethiopia*, ገፅ 181-236; World Justice ፕሮጀክት (2020). Rule of Law Index: https://worldjusticeproject.org/rule-of-law-index/factors/2020/Ethiopia/ ((በመጠረሻ የታየው: March 30. 2020 እ.ኤአ.)

የዓለም ዓቀፍ የጠበቆች ማህበር (ዓ.ጠ.ማ.) በኢትጵያ እየተደረገ ባለው የለውጥ ሂደት ውስጥ ተሳታፊ እንዲሆን ያደረጉት ዋነኞቹ ምክንያቶችም በፍትህ ስርዓቱ ውስጥ ሙስናንና መድሎን ለማስቀረት እየተደረጉ ያሉ ጥረቶችና የጥረቶቹ አንድ አካል የሆነው በሃገሪቷ የህግ ሙያን ለማዘመን እየተቀረፀ ያለው አዲስ አዋጅ ናቸው።

## 2. የዓለም ጠበቆች ማህበር (ዓ.ጠ.ማ.)

በዓለም ዙሪያ የሚገኙ የህግ ባለሙያዎች ድምፅ የሆነው የዓለም ዓቀፍ የጠበቆች ማህበር በኢትዮጵያ የህግ ሙያን የሚገዙ የህግ ማዕቀፎችን ለማዘመንና ሙያውን ለህዝብ ጥቅም ሲባል ነፃና ገለልተኛ በሆነ መልኩ እንዲተዳረር ለማስቻል እየተተገበሩ ያሉ ጥረቶችን ለመደገፍ ዝግጁ ነው።

የዓለም ዓቀፍ የጠበቆች ማህበር ከተቋቋመበት እ.ኤ.አ.1947 ዓ.ም. ጀምሮ የህግ የበላይነትን በመደገፍ በዓለም ዙሪያ ስላምና ደህንነት እንዲሰፍን የራሱን አስተዎፅዖ ሲያበረክት ቆይቷል። የዓ.ጠ.ማ. 80 ሺህ የህግ ባለሙያዎችና የህግ አገልግሎት የሚሰጡ ድርጅቶች እንዲሁም ከ170 ሃገራት የተውጣጡ ከ190 የሚበልጡ የህግ ባለሙያዎች ማህበራትን በአባልነት ያቀፈ ተቋም ነው። ለህግ ሙያ በዓለም ዓቀፍ ደረጃ እንደእናት ተቋምነቱ (global umbrella organization) ዓ.ጠ.ማ. በብዙ ሃገራት የፍቃደኛ አባልነት ወይም በህግ አስገዳጅ የሆነ አባልነት ያላቸው የህግ ባለሙያዎች ማህበራትን ምስረታን ደግፏል። የዓ.ጠ.ማ. ለረዥም ጊዜ የማህበራችን አባል ከሆነው ከኢትዮጵያ የህግ ባለሙያዎች ማህበር (ኢ.ሕ.ባ.ማ) የቆየ ግንኙነት ያለው ሲሆን ኢ.ህ.ባ.ማም በአሁን ሰዓት በኢትዮጵያ በህግና ፍትህ ስርዓት ማሻሻያዎች ላይ እየተደረጉ ያሉ ውይይቶችን በማደራጀት ረገድ ቁልፍ ሚና እየተጫወተ ይገኛል።

ኢ.ሕ.ባ.ማ. በ2012 ዓ.ም. ዓ.ጠ.ማ. በኢትዮጵያ ፍትህ ስርዓቱን ለማሻሻል እየተወሰዱ ያሉ እርምጃዎች ላይ ሙያዊ ምክሩን እንዲለግስ ጥሪውን አቀረበ። ዓ.ጠ.ማ. ጥሪውን በመቀበል በአማካሪ ምክር ቤቱ ረቂቅ ህግ እንዲያዘጋጅ ለተቋቋመው የስራ ቡድን ድጋፍ ሲያደረግ ቆይቷል። ዓ.ጠ.ማ. ለስራ ቡድኑ ከሰጣቸው ድጋፎች መካካል ፍትህ ስርዓትን ከማሻሻል አንፃር ከተለያዩ ሃገራት ተሞክሮ የተገኙ ምርጥ ተሞክሮዎችን ማሰባሰብ አንዱ ነው። የዓ.ጠ.ማ. ልዑክ በመጋቢት 2011 ዓ.ም. አትዮጵያን የጎበኘ ሲሆን በዋና ከተማዋ አዲስ አበባና ሌሎች የሀገሪቱ ክፍሎች ከሚገኙ የተለያዩ ባለድርሻ አካላትና ህብረተሰብ አባላት ጋር ውይይቶችና አውደ ጥናቶችን አከናውኗል። በቀጣይም የዓ.ጠ.ማ. ባለሙያ[3] ባደረጋቸው የስራ ጉብኝቶች የህግ ሙያ ስለሚገኝበት ነባሪያዊ ሁኔታና ስለተጋረጡበት ተግዳሮቶች ከምሁራን፣ የህግ ባለሙያዎች፣ የፌደራልና የክልል መንግስታት ተወካዮች፣ ዳኞች፣ የግል ኢኮኖሚ ዘርፍ ላይ ከተሰማሩ ሰዎችና የሲቪል ማህበራት ተወካዮች ጋር ለመወያየት አጋጣሚ አግኝቷል።

ይህም ዓ.ጠ.ማ. ለኢትዮጲያ ነባራዊ ሁኔታ አመቺ የሆኑና የህግ ባለሙያዎች ያሉባቸውን ተግዳሮቶች ላይ ያነጣጠሩ ምክረ ሃሳቦችን እንዲሰጥ አስችሎታል።

## 3. ለህዝብ ጥቅም ሲባል የህግ ሙያን ራሱን በራሱ እንዲያስተዳደር (independent regulation) ስለማድረግ[4]

አዲሱ ህግ የህግ ሙያን የሚገዛውን የህግ ማዕቀፍ ማዘመንን፣ የህግ ባለሙያዎች የባለሞያ ማህበራትን እንዲያቋሙ ማስቻልንና በአጠቃላይ ሙያው ነፃነት እዲኖረው ለህዝብ ጥቅም ሲባል የህግ ሙያ ራሱን እንዲያስተዳድር የሚያስችል ስርዓትን መዘርጋትን ዓላማው አድርጎ የተነሳ ነው።

ይህ ማለት ግን ህጉ የህግ ባለሙያዎች ጥቅምን ብቻ ያማከለ ነው ማለት አይደለም። በተለይ የፍትህ ስርዓቱ ፍትህን የማስከበር አቅሙ ላይ ጥርጣሬ የተስፋፋባቸው ሃገራት ውስጥ የህግ ሙያ ነፃነት መኖር ከህግ ጋር

[3] ዶ/ር ኮርድ በርግማን፣ ጠበቃና የቀድሞ የጀርመን የህግ ባለሙያዎች ማህበር ዋና ስራ አስፈፃሚ

[4] ይህ ሪፖርት "ራስን በራስ ማስተዳደር" የሚለውን ሐረግ ለመጠቀም ቢመርጥም ዋናው ነጥብ የህጉ ይዘት እንጂ ህጉ ይህን ሃሳብ ለመግለፅ የመረጠው ቃል ወይም ስርዓቱን "ራስን ማስተዳደር" ወይም "የጋራ አስተዳደር" ብሎ መሰየሙ አይደለም።

በተገናኘ ተዓማኒነት ያለው መረጃ በመስጠትና የፍትህ ተደራሽነትን በማስፋት የፍትህ እጦት የሚፈጥረውን ማህበረሰባዊ ቀውስ ከማስቀረት አንፃር ከፍጸኛ አስተዋፅዎ አለው።

የፍትህ ስርዓት አስተዳደር አንድ አካል የሆነውን የህግ ሙያን ማጠናከር የፍትህ ተደራሽነትን ከማጠናከር በተጨማሪ ለኢኮኖሚ እድገትም አሉታዊ አስተዋፅዎ አለው።[5] ጠንካራ የፍትህ ተቋማት በበኩላቸው የህግ የበላይነትን በማስከበር ሃገራት ውስጣዊ ሰላም እንዲኖራቸው ያስችላሉ።

እነዚህ ሃሳቦች የተባበሩት መንግስታት ድርጅት እ.ኤ.አ. በ1990 ባወጣው የህግ ባለሙያዎች ሚና መሰረታዊ መርሆዎች (United Nations Basic Principles on the Role of Lawyers)[6] እንዲሁም የአፍሪካ ህብረት የአፍሪካ የሰብዓዊና የህዝቦች መብቶች ኮሚሽን እ.ኤ.አ. ባወጣው በአፍሪካ ፍትሃዊ የፍርድ ሂደትና የህግ ባለሙያ ድጋፍ የማግኘት መብት መርሆችና መመሪያዎች (Principles and Guidelines on the Right to a Fair Trial and Legal Assistance in Africa)[7] በተሰኙት ሰነዶች ላይ የተንፀባረቁ ናቸው። እነዚህ ሰነዶች መንግስታት የዜጎችን መሰረታዊ መብቶች ለማስከበርና የፍትህ ተደራሽነትን ለማረጋገጥ ቁልፍ የሆነውን የህግ ሙያን ነፃነትን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ የህግ ማዕቀፎችን እንዲቀርፁ ይደነግጋሉ።

በተጨማሪ በአውሮፓ አህጉር የህግ ባለሙያዎች ማህበር የሆነው ሲ.ሲ.ቢ.ኢ (CCBE) ያስጠናው ጥናት እንዳተተው "የአንድ አገር የህግ ስርዓት ውስጥ የሚገኙ ተቋማት (ህጎችና ልማዳዊ አሰራሮችን ጨምሮ) የሃገርን የኢኮኖሚ ሁኔታ በመቅረፅና በመወሰን ረገድ ከፍተኛ ሚና አላቸው። ጠንካራና ተዓማኒነት ያላቸው ተቋማት የኢኮኖሚ እድገትን የሚያፋጥኑ ሲሆን የተሻለ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ እንዲኖርም ያስችላሉ። በተጨማሪም ሃገራት

የሚኖራቸው የህግ ስርዓት መዋቅር የሚወሰነው በፓለቲካዊ ተቋማት አማካኝነት ቢሆንም እንዲሁም የፀደቁ ህጎች እንዴት

እንደሚተረጎሙ የሚወስኑት ፍርድ ቤቶች ቢሆንም የህግ ባለሙያዎች በየቀኑ በሚተገብሩዋቸው ስራዎችንና በሚወስዱዋቸው እርምጃዎች የህግ ስርዓቱ የሚይዘውን ቅርፅና ውጤታማነቱ ላይ ቀጥተኛ ሚና ይጫወታሉ"።[8]

የኢትዮጵያ መንግስት የህግ ሙያን የሚገዛውን የህግ ማዕቀፍ ለማዘመን እየወሰዳቸው ያሉት እርምጃዎች እያንዳንዱ የህግ ባለሙያና የህግ ሙያ በአጠቃላይ በፍትህ ስርዓቱ ውስጥ ላላቸውን ቁልፍ ሚና እውቅናን የሰጡ ናቸው። ተገቢና ውጤታማ የሆነ የፍትህ ስርዓት ለአዎንታዊ ማህበረሰቢያዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት የጀርባ አጥንት ነው። የህግ ባለሙያና የጠበቆች ማህበራት ከፍትህ አስተዳረርና ከሲቪል ማህበራት ስራ ጋር ቁርኝነት ያለው ቅይጥ የሆነ ሚና አላቸው። በአንድ በኩል የህዝብ ጥቅምን ማስከበር ላይ የተመሰረተ የህግ ሙያ አስተዳደር ምን እንደሚመስል እንደ ሞዴል ሆነው ሲያገለግሉ በሌላ በኩል ደግሞ ለህብረተሰቡ የፍትህ ተደራሽነት እንዲኖር ሲቪል ማህበራት የሚሰሩትን ስራ ያግዛሉ።

## 4. ህጉን የማርቀቁ ሂደት

[5] እ.ኤ.አ. 2012 ዓ.ም. የዳኞችና ጠበቆች ነፃነት ልዩ ራፖርተር ባወጣው ሪፖርት ላይ እንደሰፈረው፣ UN DOC A/67/305 አንቀፅ 30, "ነፃና ሀቀኛ የሆነ የፍትህ ስርዓት ፍትሃዊ ውድድርንና የኢኮኖሚ ዕድገትን ያበረታታል ምክንያቱም በአንድ ኢኮኖሚ ውስጥ ባለው እንቅስቃሴና ሙስናን በመዋጋት ረገድ ውጤታማ በሆነ የፍትህ ስርዓት መካከል ግልፅ የሁነ ተዛምዶ ስላለ ነው።"

[6] www.un.org/ruleoflaw/files/UNBasicPrinciplesontheRoleofLawyers.pdf (በመጨረሻ የታየው: March 28, 2020 እ.ኤ.አ)

[7] www.achpr.org/legalinstruments/detail?id=38 (በመጨረሻ የታየው: March 28, 2020 እ.ኤ.አ)

[8] የሮው, ጆርጅ እና ድከርr, ክሪስቶፈር. (2012 እ.ኤ.አ) Assessing the economic significance of the professional legal services sector in the European Union. Summary ii.

በአማካሪ ምክር ቤቱ የተቋቋመው የስራ ቡድን እስከ ታህሳስ 2011 ዓ.ም. ድረስ በኢትዮጵያ የህግ ሙያ ውስጥ ያሉ የፍላጎት (need) እንዲሁምበስራ ላይ ባለው የህግ ማዕቀፍ ይዘትና አተገባበር ላይ ያሉ ክፍተቶችን ለመለየት የሚያስችል ሰፊ ጥናት ሲያደርግ ቆይቷል። የዓ.ጠ.ማ. በበኩሉ ዓለም ዓቀፍ ህግንና ነፃነት ባለው አካል የሚመራ የህግ ሙያ ዙሪያ ያሉ ዓለም ዓቀፍ ጥሩ ልምዶችን የሚዳስስ በውጪ ባለሙያ (external expert) የተጠናከረ ሪፓርት ለስራ ቡድኑ ያስገባ ሲሆን ሪፓርቱን ያጠናከረው የውጪ ባለሙያ ለስራ ቡድኑ አዲሱን ህግ በማርቀቅ ሂደት ውስጥ አስፈላጊዉን ድጋፍ እንዲያደርግ መድቦ ተንቀሳቅሷል። በተጨማሪ የስራ ቡድኑ በዋና ከተማዋ አዲስ አበባ የቡድን ውይይቶችን (focus group discussions) አካሂዷል። ከቡድን ውይይቶቹ የተገኙትን ግብዓቶችን ከገመገመ በኋላ የስራ ቡድኑ የጥናቱን ውጤት ጥር 2011 ዐ.ም. ላይ ለአማካሪ ምክር ቤቱ አስገብቷል።

በዚህ ጥናት ላይ ከተካተቱ ዋና ዋና ነጥቦች መካከል በተላይ ቀስ በቀስ ራሱን ወደ ሚያስተዳድር የህግ ሙያ ስርዓት የመሸጋገር አስፈላጊነትን ከማሳየት አንፃር ትኩረት ልንሰጠው የምንፈልገው አንድ ጉዳይ አለ። ይህም የህግ ባለሙያዎች፣ ፍርድ ቤቶችና ሌሎች ባለድርሻ አካላት በተደጋገሚ ያነሱት የፓለቲካ ተነሳሽነት ያላቸው (politically motivated) በተለይ ስራቸው አፋኝ ከሆኑ እንደ ፀረ ሽብርተኝነት ህጉ ያሉ ህጎች ጋር ቁርኝት ለነበራቸው ጠበቆች የጥብቅና ፍቃድን መልሶ ማደስና እነዚህ ጠበቆች ላይ የሚወሰዱ የዲሲፐሊን እርምጃዎችን በተመለከተ በመንግስት አካላት የሚሰጡዋቸው ውሳኔዎችን የተመለከተ ነው። አንዳንዶች እነዚህን ውሳኔዎች ትንኮሳ በማለት ሲገልፃቸው ሌሎች ደግሞ ማስፈራሪያ ወይም አድሎዋዊ በሆነ የዲሲፐሊን ስርዓት ላይ የተመሰረቱና ጠበቆችን ብቻ ሳይሆን ዳኞችና አቃቢ ህጎች ላይ ጭምር ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ሲሉ ይገልፃቸዋል። ይህም የህግ ሙያ አስተዳደሩ እምነት እንዲያጣ የሚያደርግ ሲሆን ለጥናቱ በተደረጉ የቡድን ውይይቶችና ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር የተደረጉ ውይይቶች ላይ ተሳታፊዎች ተነሳሽነት ያለውና ነፃ የሆነ የህግ ሙያ አስተዳደር እንዲቋቋም ጥሪያቸውን አሰምተዋል።

የአማካሪ ምክር ቤቱ ጥናቱ ላይ የሰጠውን ግብረ መልስ ከሰበሰበ በኋላ የስራ ቡድኑ ረቂቅ ህጉን ወደ ማዘጋጀት ተሸጋገረ። ለዚህ ስራው እንዲረዳው የስራ ቡድኑ ከዓ.ህ.ባ.መ. ልዑክ ጋር በጋራ በመሆን በአዲስ በባ፣ በባህር ዳር

(የአማራ ብሔራዊ ክልል ዋና ከተማ) እና በሀዋሳ (የደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል ዋና ከተማ) ከተሞች ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት አካሂዷል። የህግ ሙያ ነፃነትን ማስከበር ለኢትዮጵያ ማህበረሰባዊና

ኢኮኖሚያው ዕድገት አስፈላጊ መሆኑ ላይ በህግ ባለሙያዎች ብቻ ሳይሆን ከሙያው ውጪ የሆኑ የውይይቶቹ ተሳታፊዎች ዘንድም ስምምነት እንደነበር መግለፁ አስፈላጊ ነው።

በቀጣይ ውይይቶች በተለይ የሙያ ፈቃድ አሰጣጥና ራስ ገዝ የሆኑ የሙያ ማህበራት ላይ ሊደረግ ስለሚገባው ክትትል ትኩረት ሰጥተው ውይይት አድርገውባቸዋል። በነዚህ ውይይቶች ላይ መንግስት የሙያ ፈቃድ መስጠትና አመታው እድሳት ማድረግን ሙሉ በሙሉ ለህግ ሙያው ለማስተላለፍ ፍቃደኛ እንዳልሆነ አሳውቋል።

በመቀጠል የስራ ቡድኑ የህጉን የመጨረሻ ረቂቅ በነሐሴ 2011 ዓ.ም. አስረከበ። በተመሳሳይ ጊዜ ዓ.ጠ.ማ.ና የስራ ቡድኑ (በጀርመኑ ጂ.አይ.ዜድ. በተደረገላቸው ከፊል ድጋፍ) የአቅም ግንባታ ስራ እቅድ ማውጣት ጀመሩ። በእቅዱ መሰረት በተሰራው ስራ አማካኝነት ሁሉም ባለድርሻ አካላት የህጉ ዋነኛ የፓሊሲ ዓላማ የሆነውን ጠንካራና ነፃ የሆነ የህግ ሙያን ለማጠናከር መተግበር ያለባቸው ተግባራትና ሂደቶች ላይ የጋራ መግባባት ላይ መደረስ ተችሏል። ዕቅዱ አስፈላጊ የሆኑ ቅድመ ሁኔታዎችን ሲያስቀምጥ፣ ሂደቱ ዝግመታውና ዓላማውን ለማሳካት ከ3 እስከ 5 ዓመት እንደሚፈጅ ያስቀምጣል።

ለተወሰኑ ወራት ረቂቅ ህጉን በተመለከተ ምንም ዓይነት ተጨማሪ እንቅስቃሴ ሳይደረግ የቆየ ቢሆንም ታህሳስ 2012 ዓ.ም. ላይ የፌደራል አቃቤ ህግ ቢሮ ያልተጠበቀ አማራጭ ረቂቅ ህግ አቀረበ። የፌደራል አቃቤ ህግ ቢሮ

ረቂቅ ህጉ ላይ ሰፊ ውይይት እንዲካሄድ በተከተለው አቅጣጫ ምክንያት እንዲሁም የረቂቁ ይዘት በተለያዩ ባለድርሻ አካላት መካከል ተደርሶ የነበረውን የጋራ መግባባት የሚሸረሽር የሚመስል ስለነበር በህግ ባለዉያዎች ዘንድ ከፍተኛ ውይይት ተደርጎበታል።

እስከ አሁን ድረስ በስራ ቡድኑም ይሁን በአቃቤ ህግ ቢሮው የተዘጋጁት ረቂቅ ህጎች ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ያልቀረቡ ሲሆን ሂደቱ ለጊዜው የቆመ ይመስላል። ለዚህም ምክንያት የሚኒስትሮች ምክር ቤት እንዲወያይባቸው የሚቀርቡለት ረቂቅ ህጎች ቁጥር መብዛት አንዱ ምክንያት ነው።

## 5. የዓ.ጠ.ማ. ግምገማ

የኢትዮጵያ መንግስት ረቂቅ ህጉን ለማርቀቅ የተከተለው ሂደት ለሌሎች ሃገራት አርአያ የሚሆን ነው። አማካሪ ምክር ቤት ማቋቋም፣ በህግ የማርቀቅ ሂደቱ ከጅማሮው የህግ ባለሙያዎችን እውቀት ለመጠቀም የስራ ቡድኑ አባል እንዲሆኑ መደረጉና ከህግ ሙያ ውስጥና ውጪ ያሉ ባለድርሻ አካላት አስተያየትና ምልከታዎቻቸው ተደማጭነት እንዲያገኙ የተደረገው ጥረት በሂደቱ ላይ ሁሉም አካላት እምነት እንዲያሳድሩ ለማድረግ በተለየ ሁኔታ አመቺ የሆኑ አስራሮች ነበሩ።

በተቃራኒው በፌደራል ዓቃቤ ህግ ቢሮ በኩል የቀረበው አማራጭ ረቂቅ ህግ ለተሳታፊ አካላት ድንገተኛ የነበረ ይመስላል። ሳይሻሻል ከፀደቀ የዚህ ረቂቅ ይዘት አዲሱ ህግ ሊያሳካቸው ከሚችለውና ከሚገቡ ዓላማዎች አንፃር ሲታይ ወደ ኋላ የሚደረግ እርምጃ ነው። በዓ.ጠ.ማ. እይታ የአማካሪ ምክር ቤቱ የስራ ቡድን ያዘጋጀው የመጀመሪያው ረቂቅ ህግ በሂደቱ ወቅት ስምምነት ላይ ለተደረሰባቸው የህጉ ዓላማዎች የሚመጥን ነው።

የፌደረል ጠቅላይ ዓቃቤ ህግ ቢሮ የአማካሪ ምክር ቤቱ የስራ ቡድን ያዘጋጀውን ረቂቅ ህግ ሙሉ በሙሉ ለመቀበል ዝግጁ ካለሆነ ዓ.ጠ.ማ. ነፃ የሆነ የህግ ሙያን ለመመስረት የሚያስችሉ ጠንካራ የሆኑ የህግ ማዕቀፎች ሊኖራቸቸው የሚገባቸውን አነስተኛ ይዘትን እንደ እንደሚከተለው ያቀርባል።

### ሀ. ነፃነት

**የህግ ባለሙያዎች ነፃነት**: በህጉ ውስጥ ስለህግ ባለሙያው የአሰራር ነፃነትና ሚስጥራዊነት እንዲሁም የጥቅም ግጭትን ማስቀረትን የተመለከቱ የህግ ሙያ መሰረታው መርሆዎችን የሚዘረዝር ክፍል ሊካተት ይገባል። የተ.መ.ድ. የዳኞችን የህግ ባለሙያዎች ነፃነት ልዩ ራፓርተር እንዳስቀመጡት "የህግ ባለሙያዎች ነፃነት ከዳኞች ነፃነት ጋር ተመሳሳይ መሆን ባይጠበቅበትም[9]፣ (ስራቸውን በተ.መ.ድ. የህግ ባለሙያዎች ሚና መሰረታው መርሆዎች መሰረት እንዲያከናውኑ ግን) ከውጪያዊ ተፅዕኖና ጣልቃ ገብነት ነፃ መሆን አለባቸው"።[10]

**ራስን ማስተዳደር**: ይህ ከአድሎ ነፃ በሆነ መልኩ የሙያ ፍቃድ አሰጣጥን፣እደሳን፣ እገዳና ስረዛ ስርዐትን የሚመሩ፣ ጥራት ቁጥጥርን የሚያከናውኑና ፍትሃዊ የሁነ የቅጣት ውሳኔዎች ማስተላለፍ የሚችሉ ነፃ ተቋማትን የሚያካትት ነው። በተጨማሪ ህጉ እነዚህ አካላት አስፈላጊ የሆኑ ደንብና መመሪያዎችን ማውጣት እንዲችሉ የሚያስችል የህግ ማዕቀፍ ማካተት አለበት።

---

9 የዳኞችና ጠበቆች ነፃነት ልዩ ራፖርተር ሪፖርት UN DOC A/HRC/26/32/Add.1 አንቀፅ 78.

10 የተ.መ.ድ. የህግ ባለሙያዎች ሚና መሰረታው መርሆች www.un.org/ruleoflaw/files/UNBasicPrinciplesontheRoleofLawyers.pdf (በመጨረሻ የታየው: March 27, 2020 እ.ኤ.አ.)

**የአስተዳደር ተቋማት የሚያሳልፏቸውን ውሳኔዎችና ሚወስዱዋቸውን እርምጃዎችን የሚከታተሉ ነፃና ገለልተኛ የሆኑ አካላት:** የነዚህ አካላት ስልጣን የአስተዳደር ተቋማቱ ውሳኔዎችና እርምጃዎ ህጋዊነትን መገምገም ብቻ መሆን አለበት።

### ለ. መርህ ላይ የተመሰረተ ህግ

ሕጉ በስነ ምግባር ደንብ ውስጥ የሚካተቱ ዝርዝር ጉዳዮችን የሚመለከቱ ጠቅላላ መርሆችን እንዲያጠቃልል ይመከራል።[11]

### ሐ. የጥብቅና ሙያ አገልግሎት ድርጅቶች

ኢትዮጵያ ውስጥ ባለው ነባራዊ ሁኔታ የጥብቅና ሙያ አገልግሎት ድርጅቶችን ማቋቋምን መፍቀድ ጠቃሚ የሆነ ግብ ነው። ይህ በተለይ ድንበር ዘለል የሆኑ ስራዎችን (cross border business) ለሚያከናውኑ ተቋማት የህግ ምክር ለመስጠት እንዲሁም በጥብቅና ለመወከል ከሚያስፈልገው ዓለም ዓቀፋዊ ትብብር አንፃር አስፈላጊነቱ የጎላ ነው። የኢትዮጵያ የህግ ባለሙያዎች ለንግድ ተቋት የሚሰጥ የህግ አገልግሎት በፍጥነት

ፕሮፌሽናላይዝ የመደረግ ሂደት ጋር አብሮ ለመራመድ የጥብቅና ሙያ አገልግሎት ድርጅቶችን በጋራ ማቋቋም መቻል ይኖርባቸዋል።

### መ. የሽግግር ጊዜ/የጊዜ ሰሌዳ

አሁን ያለውን ስርዓት ስርነቀላዊ በሆነ መልኩ መቀየር ምክንያታዊ ባለመሆኑና መንግስት በስራ ላይ ባለው ስርዓት የተሰጠውን ያስተዳደርና ቁጥጥር ስልጣን በቅርብ ጊዜ ውስጥ ሙሉ ለሙሉ ለማስረከብ ፍላጎት ስለሌለው አዲሱ ህግ የመጨረሻ አላማው አንድ ቀን ከመንግስት ቁጥጥርና ተፅዕኖ ሙሉ በሙሉ ነፃ ወደሆነ የህግ ሙያ አስተዳደር ስርዓት መግባት መሆኑንና ይህንንም ለማሳካት የሽግግር ጊዜ በማስቀመጥ ዓላማው በምን ያህል ጊዜና በምን ዓይነት ሁኔታዎች እንደሚሳካ በግልፅ ማስቀመጥ ይኖርበታል። የሽግግር ወቅቱ በሚመለከታቸው አካላት የጋራ ስምምነት ላይ የተመሰረተ መሆን ሲኖርበት ተለዋዋጭ ሁኔታዎችን ለማስተናገድ በሚያስችል መልኩ መቀረፅ ይኖርበታል።

## 6. መደምደሚያ

ዓ.ጠ.ማ. በኢትዮጵያ የህግ ሙያን ነፃነት ለማጠናከር እየተደረገ ባለው ጥረት ውስጥ ተሳታፊ የሆኑ ሁሉንም ግለሰቦችና ተቋማት ለማመስገን ይወዳል። ዓ.ጠ.ማ. ሂደቱ ላይ ያጋጠሙ እክሎች እንዳሉ ቢገነዘብም ከአለም አቀፍ ህግና መልካም ተሞክሮዎች አንፃር መወሰድ ያለባቸው ማሻሻያዎችን ከግንዛቤ በማድረግ የህግ ሙያ ነፃነትን ለማጠናከር አስፈላጊ የሆኑ እርምጃዎችን ማሳካት እንደሚቻል ያምናል። እነዚህ ስኬቶችም በተራቸው በኢትዮጵያ የፍትህ ተደራሽነት፣ ዲሞክራሲያዊ አስተዳደር፣ ኢኮኖሚያዊ ዕድገትና የህግ የበላይነት እንዲሻሻል የራሳቸውን ድርሻ ያደርጋሉ።

የተጀመረውን ሂደት ለመደገፍና ለኢ.ሕ.ባ.ማ. ይሁን ለአማካሪ ቡድኑ ላቋቋመው የስራ ቡድን አስፈላጊውን እርዳታ ለማድረግ አሁንም ዝግጁ ሲሆን ከኢትዮጵያ መንግስት ጋርም ለመወያየት በራችን ክፍት መሆኑን እንገልፃለን።

በመጨረሻም ዓ.ጠ.ማ. ስለኢትዮጵያና ስለተጋረጡባት ወቅታው ተግዳሮቶች መረጃ ለሰጣችሁን ሁሉ ምስጋናውን ያቀርባል። ከናንተ ጋር ስለህግ የበላያነት፣ ዲሞክራሲያዊ ሽግግርና የህግ ሙያን በተመለከተ ያሉ ምርጥ ዓለም ዓቀፍ ተሞክሮዎች መወያየታችን ተላቅ ደስታን ሰጥቶናል።

---

[11] ዓ.ጠ.□. የስነምግብር ህጉን ለማዘጋጀት የሚደረጉ ስራዎችን በሙያዊ ስነምግባር ኮሚቴው አማካኝነት ለመደገፍ ዝግጁ ነው።